# የአንድነት ዜናዎች

ጃንዋሪ 11 2010

## መድረክ በባህር ዳር ከተማ ከ5ሺህ በላይ ሕዝብ የተገኘበት ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄደ

- *ዶ/ር ነጋሶ ልዩ አቀባበል ተደረገላቸው*
- *ቡድኑም ለድርጅታዊ ስራ ወደ ታሪካዊቷ የጎንደርና ደብረማርቆስ አቅንቷል*

እሁድ እለት ጃንዋሪ 10 2010 (ጥር የመጀመሪያ ሳምንት 2002 ዓ.ም.) የሚከተሉት የመድረክ ተወካዮች ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ በባህር ዳር ስታዲየም አድርገዋል።

1. ዶ/ር መረራ ጉዲና
2. ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው
3. ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
4. አቶ ስየ አብርሃ
5. አቶ ገብሩ አስራት
6. አቶ አስራት ጣሴ

የጎጃምን የጎንደርን የወሎንና ሰሜን ሸዋን በመዲናነት የምታገለግለው የጣናዋ እንቁ ከተማ ባህር ዳር እንደሌሎቹ ከተሞች ለውጥን ስትሻ ከራርማለች። ወያኔን የሚያገለግለው የብአዴን ካድሬዎች የተኮለኮሉባት ባህር ዳር የለውጥ ነፋስ ስትሻ እሁድ እለት አንድ መድረክ አገኘች። የለውጥ ጥም ያቃጠለው ከ5ሺህ የሚበልጥ የባህር ዳር ሕዝብ ስታዲየም በመታደም እንደተወዳጁ እግር ኳስ የመድረክ ተወካዮችን ሲመለከት–ሲያዳምጥ–ሲያጨበጭብ–እልል ሲል–ደስታውን ሲገልጽ ዋለ። ስምብሰባዉን ለማስተዋወቅ ሚዲያዎችን በአግባቡ መጠቀም በማይቻልበት ሁኔታ ያን ያህል ሕዝብ በአጭር ጊዜ መለስተኛ ቅስቀሳ ብቻ መገኘቱ የመድረክን ተወካዮች ጭምር ያስደመመ ነበር።





በዚሁ እለት ጠለቅ ያለ ገለጻና ውይይት በተለያዩ አንኳር የኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይና በግፍ ስለታሰረችው የአንድነት ፓርቲ መሪ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ሁኔታ ላይ የተደረገ ሲሆን የባህር ዳር ህዝብም በጋለ ሆታና ጭብጨባ ድጋፉን ሲገልጽ ውሏል። ከቀኑ ክንዋኔዎች አንዱ ከፍ ያለ የሕዝብ እልልታ የቀለጠለት ጉዳይ የዶ/ር ነጋሶ አቀራረብ ነበር። የቀድሞው ፕሬዚደንት በወያኔ ክፍፍል ወቅት ለሕዝብ በቀረበ የቴሌቪዥን ክርክር የወያኔውን መሪ *"መንግስቱን መሰልከኝ"* በማለት በድፍርታቸው የጀመሩትን የተቃውሞ ጉዞ የኢትዮጵያን ሕዝብ በድያለሁ ይቅርታም እጠይቃለሁ በማለታቸው ታላቅ ከበሬታንና ተቀባይነትን ከሕዝብ እያገኙ ይገኛሉ። በባህር ዳርም የታየው ይኸው ታላቅ የሕዝብ አርቆ አስተዋይነትና ይቅርባይነት ነበር።

የአንድነት ፓርቲ አመራሮች ቀጣይ ሕዝባዊ ስብሰባ ከሚያደርጉባቸው አንዷ ወደ ሆነችው የጎንደር ከተማ ለድርጅታዊና መሰናዶ ስራ ዘልቀዋል። ከዚሁ በተያያዘም መድረክና አንድነት አዲስ አበባን ጨምሮ በመላ የኢትዮጵያ ታላላቅ ከተሞች ሕዝባዊ ውይይቶችን በተከታታይና በስፋት እንደሚያደርጉ ታውቋል።





## የከምባታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅትና አባላቱ አንድነትን ተቀላቀሉ የአንድነት አመራርም በሆሳአና የተሳካ የአባላት ስብሰባ ተካሄደ።

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ህዝባዊ መሰረቱ በመላ ኢትዮጵያ ስር እየሰደደና እየሰፋ እንደመጣ የሚያረጋግጡ ውጤቶች እየተመዘገቡ ነው። አንድነት ፓርቲ መዋቅር ዘርግቶ በብዙ የሃገራችን ክፍል ካደራጃቸው ጽህፈት ቤቶች በተጨማሪ ቢሮ በኦፊሴል ያልተከፈተባቸው አካባቢዎች እራሳቸውን እያደራጁ ድርጅቱን ወደነሱ በመጋበዝ ሕዝባዊ ተቀባይነቱንና የሕዝቡን ተነሳሽነት መስካሪ በመሆን ይገኛሉ።

በቅርቡ በሃድያ ዞን በሆሳዕና ከተማ ተጨማሪ ድል ተመዝግቧል። ከምንም በላይ ኢትዮጵያዊነትን ማዕከል አድርጎ የተነሳው የአንድነት ፓርቲ ለሃገራችን ምስቅልቅል ፓለቲካ ትክክለኛ መንገድ ስለመሆኑ እየተመዘገቡ ያሉት ድሎች ይመሰክራሉ። በብሄር ፓለቲካ እረጅም ጊዜ ያሳለፉት የቀድሞው ፕሬዚደንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና የቀድሞው የመከላከያ ሚኒስትር አቶ ስየ አብራሃ አንድነት ፓርቲን መቀላቀላቸው የቅርብ ጊዜ ክንውን ነው። አሁን በማስከተል ደግሞ የከምባታ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ከነመሪዎቹና አባላቱ በሙሉ የአንድነት ፓርቲን ተቀላቅለዋል። በደቡብ ክልል የሚገኘው የከምባታ ህዝብ ወደ 2 ሚሊዮን እንደሚሆን ሲገመት የወያኔ መንግስት ከገባ ጀምሮ የከረረ ተቃውሞውን ባገዛዙ ላይ በተግባር ሲያሳይ እንደቆየ ይታወቃል። እጅግ አፈና በበዛበት ያለፉት የኢትዮጵያ ምርጫዎች እንኳን የከምባታ ህዝብ የራሱን ተወካዮች በመምረጥና ድሉም እንዳይነጠቅ በማስጠበቅ አንጸባራቂ ድል ሲያስመዘገብ ቆይቷል።

ጃንዋሪ 9 2010 (ጥር መጀመሪያ ሳምንት 2002 ዓ.ም.) ከፍተኛ የአንድነት ፓርቲ አመራሮች የሆኑት

1. የአንድነት አዲስ ወጣት ዋና ጸሃፊ አቶ አንዱአለም አራጌ
2. የድርጅቱ የጥናትና ምርምር ሃላፊ ዶ/ር ሃይሉ አርአያ፤
3. የሴቶች ጉዳይ ሃላፊ የሆነችው ላቀች ደገፋ ወደ ሆሳዕና ከተማ አምርተው ነበር።

ከላይ የጠቀስነው የከምባታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅትን ወደአንድነት መቀላቀል በተመለከተ ከአባላትና ደጋፊዎች ጋር አመርቂ ውይይትና ምክክር አድርገዋል። ተሰብሳቢው ***የከምባታ ሕዝብም መምረጥና ማሸንፍን ብቻ ሳይሆን ድላችንንም ማስጠበቅ በሚገባ እናውቅበታለን በማለት ቢጋለ ስሜት አረጋግጠዋል***። ምርጫ 97ን በማሸነፍ ስድስት የፓርላማ መቀመጫን የያዙት የከምባታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ተወካዮች የድርጅቱን አባላትና ደጋፊዎች ይዘው ሙሉ በሙሉ ከአንድነት ፓርቲ ጋር በመቀላቀል ለማያዳግም ድል ዝግጅት በማድረግ ላይ ተጠምደዋል። ተመሳሳይ የውህደት ጥያቄዎች ከሌሎች ፓርቲዎች እንደሚመጣም ይገመታል።